# በአማሮ ልዩ ወረዳ በኹለት ቀበሌዎች ሸኔ የከባድ መሣሪያ ጥቃት መክፈቱ ተገለጸ

By **ኢዮብ ትኩዬ** - 23/07/2022

***ኹለት ሰዎች ሲገደሉ አምስት ቆስለዋል***

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል አማሮ ልዩ ወረዳ የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች ከተለመደው በተለየ መልኩ በነዋሪዎች ላይ የከባድ መሣሪያ ጥቃት መክፈታቸውን ነዋሪዎቹ ለአዲስ ማለዳ ገለጹ።

የከባድ መሣሪያ ጥቃቱ የተከፈተው በአማሮ ልዩ ወረዳ ስር በሚገኙ ሸሮ እና ጀሎ በተሰኙ ኹለት ቀበሌዎች መሆኑን አዲስ ማለዳ ከአካባቢው ነዋሪዎች ሰምታለች። ኦነግ ሸኔ በከፈተው ጥቃት ይህ ዘገባ እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ፣ ኹለት የሸሮ ቀበሌ ነዋሪዎች መገደላቸውን የዐይን እማኞች ለአዲስ ማለዳ ተናግረዋል።

ሟቾቹ ይድናሉ ተብሎ ወደ ሐኪም ቤት ሄደው ቢቆዩም፣ የደረሰባቸው ጉዳት ከባድ በመሆኑ መዳን እንዳልቻሉና ከአንድ ቀን ቆይታ በኋላ፤ ማለትም ሐምሌ 14/2014 በሸሮ መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን የቀብር ሥነ ሥርዓት እንደተፈጸመላቸው ምንጮች ገልጸዋል። የአዲስ ማለዳ ምንጮች እንደገለጹት ከሆነ፤ የሟቾችና የተጎጂዎች ቁጥር ከዚህ ሊያሻቅብ እንደሚችል ነው።

ታጣቂዎቹ በነዋሪዎቹ ላይ የግድያ ጥቃት ያደረሱት ባሳለፍነው ሐምሌ 13/2014 ሲሆን፤ በስፍራው የነበረው የመከላከያ ኃይል ከ30 አይበልጥም ነበር ተብሏል። የመከላከያ ኃይል ቁጥር አናሳ መሆኑን ተከትሎም ታጣቂ ቡድኑ ጥቃት ሲሰነዝር ነዋሪውን ትተው ነው የሸሹት ተብሏል። ኦነግ ሸኔ ሰዎችን ከመግደሉ በተጨማሪ ከ70 በላይ የሚሆኑ የአርሶአደር ከብቶችን እንደነዳም ተመላክቷል።

በሌላ በኩል ከሐዋሳ እስከ ዲላ፤ ከዲላ እስከ አማሮ የሚወስደው መንገድ ከተዘጋ ሰባት ዓመት እንዳስቆጠረና እስከ አሁን እንዳልተከፈተ ጠቁመው፤ መንግሥት ግን ይህ ሁሉ ጊዜ እስከሚፈጸም ዝም ብሎ ዕያየ ነው ብለዋል።

ሸኔ ከሰባት ዓመት በፊት ጀምሮ እስካሁን ድረስ በአማሮ ልዩ ወረዳ ጥቃት ማድረሱን አላቆመም ያሉት የጀሎ ቀበሌ ነዋሪ፤ ከዚህ የባሰ ሳይመጣ ቢያንስ እንኳ በርከት ያለ የመከላከያ ኃይል እንዲመድብላቸው አሳስበዋል።

---

**ተጨማሪ ጽሑፎች፡**

- በሰሜን ሸዋ ዞን ደራ ወረዳ ንጹሐን ዜጎች በታጣቂዎች መገደላቸው ተነገረ
- የሲዳማ ክልል መሆን እና ይዞ የሚመጣው መዘዝ
- የኦዴፓ እና ኦነግ ጫማ መለካካት! “የኦነግ ሠራዊት” ለዳውድ ኢብሳ ይታዘዛል ወይ?

---

ምንጮች እንደገለጹት ከሆነ፤ ይህ በሆነ በማግስቱ ማለትም ሐምሌ 14/2014 ደግሞ ታጣቂ ቡድኑ በወረዳው ስር በምትገኘው ጀሎ ቀበሌ ባሉ ነዋሪዎች ላይ የከባድ መሣሪያ ጥቃት ከፍቷል።

ጀሎ ቀበሌ አሁንም ቢሆን በጥቃት ቀጠና ውስጥ መሆኗን ተከትሎ ሙሉ ለሙሉ የደረሰው ጉዳት ባይታወቅም፣ እስካሁን የአካባቢው ነዋሪዎች ባላቸው መረጃ መሠረት አምስት ነዋሪዎች ቆስለዋል።

በመሆኑም አረጋውያንና ሕጻናትን ጨምሮ በየተራራው ተበታትነው እንደሚገኙና ከእነዚህም መካካል አንዱ ስለመሆናቸው መረጃ አቀባዩ ለአዲስ ማለዳ መስክረዋል።

ወረዳው የጥቃት መናኸሪያ ነው የሚሉት የአካባቢው ነዋሪ፤ ሰሞኑን ጥቃት የተከፈተበት ጀሎ ቀበሌን ጨምሮ እስካሁን በ10 ቀበሌዎች የነበሩ ሰዎች በታጣቂ ቡድኑ ሲገደሉ፤ ሲፈናቀሉና ንብረታቸው ሲዘረፍ ቆይቷል ሲሉ አስታውሰዋል። አሁንም ቢሆን ጀሎ ቀበሌን የከባድ መሣሪያ ተኩስ አጅቧታልም ብለዋል። ሐምሌ 14/2014 ከቀኑ ሰባት ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ተኩልም ያለማቋረጥ የተኩስ ልውውጥ መደረጉን ከቦታው በቅርብ ርቀት የሚገኙ የአካባቢው ነዋሪ ለአዲስ ማለዳ ተናግረዋል።

አዲስ ማለዳ ያነጋገረቻቸው የአማሮ ልዩ ወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ ታረቀኝ መላኩ፤ የኦነግ ሸኔ ታጣቂ ቡድን ከዚህ በፊት ጥቃት ሲፈጽም መቆየቱን አንስተው፤ አሁንም ጀሎ ቀበሌን በቁጥጥር ስር ለማድረግ ጥቃት መክፈቱን ተናግረዋል፡፡ አስተዳዳሪው ባሉበት ስፍራ የተኩስ ልውውጥ መኖሩን ተናግረው፤ ከዚህ በላይ ምላሽ መስጠት እንደማይችሉ ገልጸዋል፡፡

የወረዳው ሰላምና ፀጥታ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ብሩክ አየለ በበኩላቸው፤ ከአዲስ ማለዳ ጋር እየተነጋገሩበት በነበረበት ወቅት፣ ያሉበት አካባቢ ታጣቂዎች በመኖራቸው ጉዳዩን ለማብራራት እንደማይመች ተናግረዋል፡፡

---

ቅጽ 4 ቁጥር 194 ሐምሌ 16 2014

**ኢዮብ ትኩዬ**

*https://addismaleda.com/*

## ስለ እኛ

አዲስ ማለዳ ወቅታዊ የአገራችንን ጉዳዮች በስፋትና በጥልቀት የምትተነትን፣ እንዲሁም የተረጋገጡና የትም ያልተሰሙ ዜናዎች የሚቀርቡባት የብዙኃን መገናኛ ናት፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚዲያ ባለስልጣን በመዝገብ ቁጥር 241/2010 ተመዝግባለች፡፡

ያግኙን: info@addismaleda.com

## ይከታተሉን

© Addis Maleda 2023 a CHAMPiON Communications Publication